# <u>ፍቅርና ሌብነት</u>

ስማቸው ይባላል ደፋሩ ጎሽሜ
የስልሳ አመቱ ጎረምሳ የእንጦጦው ከተሜ ፤
ከተማ መጎብኘት ያሰኛቸው ለታ
ተወዳጆቻቸው ሲያምራቸው ጨዋታ
ክትፎ ቤት አትጠፋም ሰወር ካለች ቦታ።
ይህች ሱሱቸው የተነሳች ለታ
ይደራርቡና ጥበብና ኩታ፤
መከለያ ቢጤም ላናት ላይ መላጣ
ደፋ ያደርጉና ኮፍያ ባርኔጣ፤
ይኮረኩሩና አሮጌዋን ታኑስ፤
ወደ ሸገር መኽል፥ እልም ይላሉ እብስ።
ታዲያማ ፥ አንድ'ኛ ይችኑ ለማድረስ
ጨዋታ ፍለጋም ለመበቀል ንፋስ
አካልን አዝናንቶ መንፈስን ለማደስ
ከላይ ሽሮሜዳ ቁልቁለቱን ወርደው
ሰማዕታት ሃውልቱን 6 ኪሎን አልፈው ፤
ጉዞ እንደጀመሩ፥ ወደ 4 ኪሎ
አይናቸው ታርፋለች፥ ካንዲት ሸጋ መሳይ፥
ጠምበለል መለሎ።
አጠገብዋ ደርሰው፥ ፈገግ እንደማለት፥
በርም እንደመክፈት
ከመጣታቸው፤
ከጎናቸው ገብታ አስደተቻቸው።
ፈገግታም ለማፍለቅ ሞከር አድረገው
ጥርስ እንደሌላቸው ትዝ ሲላቸው
እንዲህ አሉ ወዲያው ሃሳብ ለውጠው።
ወዴት ነው መሂጃሽ፥ የያዝሽው ጎዳና ?
ቤህ በጣይ ጉዞ መች ይገፋልና
እረፍት ቢጤ እናድርግ መንገዱ እንዲቀና
ለምን አንቀምስም ሻይ ቢጤ ወይ ቡና ? "
በማለት ልጅትን ይጠያቃይሉ
እንደ መጎንተልም እየከጃጀሉ።
ልጅት ያራዳ ነች አይደለች ዋዘኛ፤
ፈገግታ አክላበት በጉራማይሌኛ
ፋንታስቲክ ! ነበረ፥ ግን ይረፍድብኛል
ኔቨር ካልኩ ደግሞ፥ ዳድ ይቆጡብኛል።
ኦኬ! ነኝ እንቀጥል ይበሉ እንሂዳ፤
መቼም ጨዋ ሰው ኖት፥ ያከብራሉ እንግዳ።
ለጨዋነቱማ መች አነሰኝ ብለሽ
ከቦታው ስንደርስ ትታዘቢኛለሽ ፤
ላይ ላዩን ቢዋሹም፥ ውስጥ ውስጡን ተግባብተው
ክትፎው ቤት ደረሱ ከደምበኞቻቸው።

በጭብጨባ ቢጤ አስተናጋጅ ጠርተው
በጆሮ ሹክሹክታ ፥ በጥቅሻም ብለው
ውለታ መክፈያ፥ ጉርሻ መሳይ ጥለው
መኝታ ቤት ገቡ ተዘጋጅቶላቸው።
ክትፎውም ተበላ፥ ውስኪውም ተጠጣ
እንዲሁም አለቀ ያልጋ ላዩም ጣጣ።
ያራዳዋ ቆንጆ አቀረበች ሃሳብ
መንፈስን ለማደስ ለማጠንከር ወገብ፤
ሻወር መፍትሄ ነው ካልጋ ላይ ይውረዱ
ብላ ስትላቸው፤
እንዴት ያለች ሸጋ አጋጠመኝ ዛሬስ
ተፍቅር ጭማሪ ምክር የምትለግስ
እያሉ ደፋሩ ሲዘፈቁ ገንዳ
ይፈተሽ ጀመረ የኮታቸው ጓዳ
በዚያች በቆንጆ ልጅ በዚያች በአራዳ ።
አራቆተቻቸው ሣንቲምም ሳታስቀር
ሳይለቃለቁ ሳይወጡ ከሻወር
ወሰደችባቸው ምንም ሳታቅማማ
በሩን ዘግታባቸው ኮቴ ሳታሰዊ፤
እልም ጭልጥ አለች፥ ወደ አዲስ ከተማ።
ሴሰኛው አዛውንት አባባ ደፋሩ ፤
ወይ ጊዜ፥ ወይ ጊዜ፥ ጊዜ ባለ ውሉ፤
ሌብነትና ፍቅርን አስማማ ቸው አሉ ።
የሚለውን ዜማ እያንጎራጎሩ
ያችኑ ታኖስዋን እያንኮራኮሩ ፤
ሽቅብ ሽሮሜዳን ዳገቱን ጀመሩ።

ከጌቱ ሀይሉ